

# የተባበሩት መንግስታት ስነ-ህዝብ ፈንድ ኢትዮጵያ ሀገራዊ ፕሮግራም (2020-2025)

ሙሉ ሪፖርቱን *unfpa.org/evaluation* ላይ ያንብቡ


እ.ኤ.አ. ከሀምሌ 2020 እስከ ሰኔ 2025 ዓ.ም. ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለው የተባበሩት መንግስታት ስነ-ህዝብ ፈንድ ኢትዮጵያ 9ኛ ሀገራዊ ፕሮግራም ለውጥን ለማራመድ ያለሙ ስድስት ዋና ዉጤቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ፕሮግራም ነው፤ እነዚህም፡- (1-2) ጠንካራና ጥራቱ የተጠበቀ እንክብካቤና አገልግሎቶች፣ (3) ስነ-ፆታና ማህበራዊ ልማዶች፣ (4) የስነ-ህዝብ ለዉጥና ዳታ፣ (5) ሰብአዊ ድጋፍ፣ እና (6) አፍላ ወጣቶችና ወጣቶች ናቸው።

የሀገራዊ ፕሮግራሙ ግምገማ አላማ የፕሮግራሙን አፈፃፀም መመዘን፣ ተጠያቂነትን ማሳደግና፣ በባለድርሻ አካላት ዘንድ በጎ ተሞክሮን መቅሰምና መረጃ ላይ የተመረኮዘ ውሳኔ ሰጭነትን ማበረታታት ነው።

ትንተና እና ቅይጥ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ያዋለ ንድፈ ሀሳባዊ ግምገማ ተካሂዷል፤



**160** የባለድርሻ አካላት ተወካዮች በመረጃ ሰጪ ቃለመጠይቆች አማካኝነት መረጃ ሰጥተዋል፤




አግባብነት፣ ቅንጅት፣ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና፣ ዘላቂነት፣ ትብብር፣ የፕሮግራሙ ሽፋንና ተያያዥነት ከግምት ውስጥ ገብተዋል፤

በፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ **30** ሰዎች በቡድን ውይይት ተሳታፊ በመሆን መረጃ ሰጥተዋል፤

**ከ70+** በላይ ሰነዶች ተገምግመዋል፤



**5** ምልከታዎችም ተካሂደዋል።

# ቁልፍ ነገሮች

- ፱ኛው ሀገራዊ ፕሮግራም ቅድሚያ ከተሰጣቸው ብሄራዊና ዓለምአቀፍ ጉዳዮች ጋር የተጣጣመ ቢሆንም ዘላቂነትን ከማረጋገጥ አንፃር ግን የአገራዊ ስርአቶችን አቅም የበለጠ ማጠናከር ያስፈልጋል፤
- የስነ-ተዋልዶ ጤናን በማሻሻልና ፆታዊ እኩልነትን በማስፈን ረገድ የተባበሩት መንግስታት ስነ-ህዝብ ፈንድ ትብብሮችን በማጠናከር በትብብር ማእቀፎች ውስጥም ንቁ ተሳትፎ የነበረዉ ቢሆንም በትብብር ላይ ክፍተቶች ይታያሉ፤
- አንዳንድ ከተስተዋሉ የበጀት ክፍፍል ችግሮች በስተቀር የሰው ሀብትና የገንዘብ ድጋፎች በሚገባ ጥቅም ላይ ዉለዋል፤
- የክትትልና ግምገማ ስርአቱ ጠንካራ ነበር፤ ነገር ግን መረጃ አያያዝና እውቀት አጠቃቀም ላይ ልዩ ትኩረት ያሻል፤
- የሰብአዊ ምላሽ አቅምን በተመለከተ ጉልህ መሻሻል ታይቷል፤ ነገር ግን እገዛ የሚያስፈልጋቸዉን የህብረተሰብ ክፍሎች በተሻለ ሁኔታ ለመለየት፣ እንዲሁም የሰብአዊ ምላሽ፣ ልማትና ሰላም ጥምር ሂደት ትግበራ ላይ የሰላም ክፍሉን በማካተት ረገድ የተሻለ መሰራት ይኖርበታል፤
- የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት አቅምን በማጠናከር የተሻለ መስራት ቢቻልም የፕሮግራም አካታችነትና አፈፃፀም ላይ ተግዳሮቶች ተስተዉለዋል፤
- የወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና እና ኤችአይቪ መከላከል ላይ በአካታችነት የተሰራ ቢሆንም የተገኘዉ ዉጤት ላይ በመመርኮዝ የወጣቶች ውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎን ማበረታታት ያስፈልጋል፤
- ሀገራዊ ፕሮግራሙ የፆታ እኩልነትን ለማራመድ ያላሰለሰ ጥረት ያደረገ ቢሆንም ስር የሰደዱ ጎጂ ማህበራዊ ልማዶችና ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ያለዉ የዳታ እጥረት እንቅፋት ፈጥረዋል፤
- ፱ኛው ሀገራዊ ፕሮግራም የሀገሪቱን የዳታ ስርአት ለማጠናከር ያደረገው አስተዋፅኦ እንዲሁም ለህዝብና ቤት ቆጠራ መካሄድና ለስነ-ህዝብ ፖሊሲው ክለሳ ሲያደርግ የቆየው አድቮኬሴ ተጠቃሽ ናቸው።

# ምክረ ሀሳቦች

## ስትራቴጂክ

- ለፖሊሲ ትግበራና ክትትል ትብብሮችንና አገራዊ አቅምን ማጠናከር፤
- ከመንግስት፣ ከተባባሩት መንግስታት በኢትዮጵያ፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ከልማት አጋሮች ጋር ትብብርን ማጠናከር፤
- የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል፤
- መረጃን መሰረት ላደረገ ዉሳኔ አሰጣጥ የእዉቀት አጠቃቀም እንዲሁም ክትትልና ግምገማን ማሳደግ፤
- ሰብአዊ ቀውስን የመቋቋም አቅምን መገንባትና አካታች የሰብአዊ ምላሽ፣ ልማትና ሰላም ፕሮግራሞች ትግበራን ማጠናከር።

## ፕሮግራም

- መረጃ ላይ የተመረኮዘ የፕሮግራም አወቃቀርን ማጠናከር፣ እንዲሁም የስነ-ተዋልዶ ጤና፣ ቤተሰብ እቅድ፣ ኤችአይቪ መከላከል፣ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ምርመራ እና ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ያተኮሩ አገልግሎቶችን በተቀናጀ ሁኔታ ማስፈፀም፣
- ወጣት ተኮር ፕሮግራሞችን ማጠናከር፣ በተጨመሪም ቅንጅትን በማሳደግ የወጣቶችን የአመራርና ፖሊሲ ላይ ተፅእኖ የማሳደር አቅምን ማጎልበት፤
- ስነ-ፆታን ያማከሉ የለዉጥ አካሄዶችን በማራመድ በማህበረሰቡ ውስጥ የባህሪ ለዉጥ እንዲመጣ ማበረታታት፣ እንዲሁም የፆታ እኩልነትን ለማምጣት የህግ ማእቀፉን ማሻሻል፤
- የስታትስቲክስ ስርአቱን ማጠናከር፣ እና ስነ-ህዝብን በልማት እቅድ ዉስጥና በሰብአዊ ምላሽ ዉስጥ ማካተት።